ትዕዛዘ ቃልከሙ ይኩን አምጣነ ብሔር መሰየ ጸላኢ ኢይባዕ ውስተ ቤትየ ሥላሴ ዘከሃ ሥላሴ ዘዝየ በሰላም ኅድሩ ምስሌየ።፫ተ ጊዜያተ።
ስብሐት ለእግዚአብሔር በል። ጸሎተ ሃይማኖት በል።

## ሰላመ ማርያም ዘሌሊት

ሰላም ለኪ ማርያም ሰብሕት ቀስተ መሐላሁ ለኖኅ ውስተ ገጸ ምድር ዳግመ እምደመና ላሕ ኢያንጠብጥብ ዝናመ አይኅ ሰላም ለኪ።

ማርያም ኆኅር ወላዲተ ክርስቶስ መና እንበለ ፋካቤ ወዘርዕ በድንግልና በገዳም ወበሐቅለ ሲና ሰላም ለኪ።



የቃላችሁ ትዕዛዝ ይፈጸም ዘንድ ጊዜ ስለመሸ ጠላት ወደ ቤቱ እንዳይገባ የዛሬና የቀድሞ ጌቶች ሰሉስ ቅዱስ ሆይ በፍቅር ከእኔ ጋር እደሩ።3ት ጊዜ።
ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና በል። የሃይማኖት ጸሎት በል።

## በሌሊት የሚጸለይ የእመቤታችን ሰላምታ

ከደመና ልቅሶ የጥፋት ዝናም ዳግመኛ በምድር ፊት ላይ እንዳይወርድ ያቆምሽ የኖኅ የመሐላው ምልክት የሆንሽ የተመሰገንሽ እመቤታችን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል።

በሲና የዱር በረሃ ውስጥ ያለዘርና ያለ ፋካቤ በድንግል መና ክርስቶስን ያስገኘሽ ኆሞር እመቤታችን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል።

ለሊቀ ካህናት አሮን ማርያም ልብሱ ወጸናጽለ ወርቅ ዘብኪ ዘስከዕት በናዕሱ ከመ ትድምፂ ጊዜ ያንሶሱ ሰላም ለኪ።

ማርያም ርግብ ዘወደሰኪ መጽሐፍ በሐመልማለ ወርቅ ጽሩይ ወብሩር ንጡፍ ሥርጉተ ገበዋት ምስለ አክናፍ ሰላም ለኪ።

ማርያም ገነቱ ለወልደ ኢያሬጥ (ያሬድ) ወሬዛ ዘተተክለ ብኪ ኢየሱስ ለቤዛ ፍሬ ጽድቅ ምስለ መዐዛ ሰላም ለኪ።

ማርያም ባሕርይ ጽድልተ ንጻሬ ወዜና እምጸዳለ ፀሐይ ወወርኅ በማኅፀና ዘትወልድ የፌ ብርጋና ሰላም ለኪ።

ማርያም ሀብኒ ልብሰ ትፍሥሕት ወተድላ ከ
ወሀብኪዮሙ ቅድመ ልብሰ መሐላ ለደቅስዮ
ወለኒቆላ ሰላም ለኪ።

ቅድሜየ ቁሚ ማርያም ለለጊዜ እቀብጽ ተሰ
የፌ ተእምርኪ ርግብ እንዘ ትሰፍህ ክንፋ ከ
ቆመት ቅድመ ከሊፋ ሰላም ለኪ።

ማርያም አብሕኒ ዘአባሕኮሙ ሶበ ኃቢኪ ጸለ
መነኮሳት ዘግብጽ/ለመነኮሳተ ግብፅ/ መጠ
ሐለዩ ሰይጣነ ከመ ይቅንዩ ሰላም ለኪ።



እመቤቴ ሆይ ለደቅስዮስና ለኒቆላ የመሐላ ልብስን እንደሰጠሻቸው የተድላና የደስታ ልብስን ትሰጪኝ ዘንድ ሰላም እልሻለሁ።

እመቤቴ ሆይ የተአምርሽ ወፍ እርግብ በእስላሙ ንጉስ ፊት ክንፏን ዘርግታ እንደቆመች ተስፋ ባጣሁ ጊዜ በፊቴ ትቆሚ ዘንድ ሰላም እልሻለሁ።

እመቤቴ ሆይ የግብጽ መነኮሳት ሰይጣንን ይገዙ ዘንድ እንዳሰቡ ወደ አንቺ በለመኑ ጊዜ እንደ አሰለጠንሻቸው እኔንም ታሰለጥኚኝ ዘንድ ሰላም እልሻለሁ።

ወልድኪ ንፍሳተ ሰብ አርአየኪ በእሳተ ኲነኔ
ዘሐሙ ማርያም ትብሊ በእንቲአሆሙ ትትለነ
ለቤዛሆሙ ሰላም ለኪ።

በእማዕንኪ ማየ ዘአስተይኪዮ ለጽሙዕ ከልብ
ከመ ተራኅራኅኪ ቅድመ ማርያም ርግብ
ተራኅርኂ ለቤዛ ሕዝብ ሰላም ለኪ።

ማርያም ጸግዊ ለደቂቀ ዛቲ ምስያ
እምንዋየ ጽድቅ ብዙኅ ወእኮ ኅዳጥ እመ
ይጸርዕ መዋዕለ ሴጥ ሰላም ለኪ።

ድካመ ጌጋይየ ትማዕ ማርያም ጽድቀ ዚአ
በጽንእ መዳልወ ጥበብ ሰበ መልዓ ከመ ሰማኔ
ንፍሳተ ወሰብዓ ሕፍን ማይ ኅየለ ወሞዐ።

፫ተ ጊዜያተ በል።



ልጅሽ በሲኦል ውስጥ የተፈረደባቸውን ነፍሳት በአሳየሽ ጊዜ ስለእነርሱ ድነት እኔን ግደለኝ የምትዪ እመቤታችን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል።

የተጠማውን ውሻ በጫማሽ ውሃን ያጠጣሽ እምቤታችን ሆይ ቀድሞ እንደራራሽ ሕዝብን ለማዳን ትራሪ ዘንድ ሰላምታ ይገባሻል።

እመቤታችን ሆይ የገበያው ጊዜ ከማብቃቱ አስቀድሞ ጥቂት ያይደለ ከብዙ የጽድቅ ገንዘብ ለዚህች አደባባይ ልጆች ትሰጪ ዘንድ ሰላም እልሻለሁ።

ሰባ ስምንት ሰዎች የበላውን ሰው ለማዳን የጥበብ ሚዛን በሞላ ጊዜ ጥርኝ ውሃ በርትቶ እንዳሸነፈ እመቤቴ ሆይ የእንቺ ጽድቅ በኃይሏ በደሌንና ድካሜን ታሸንፍልኝ።

3ት ጊዜ በል።

ደዌነ ነሣዕከ **ወሕማማቲነ** ፆርከ ከመ ተነበ
ነቢያተ ዚአከ ኃጢአት እንዘ አልብከ ስ.ለከ።

**መንፈቀ ሌሊት** ድኅረ ጊዜ ይከውን ወው
ቤተከ ነህሉ በተጋብኦ ሶበ ሰአልናከ በአስተ
በቍየ አርኅወነ እግዚእ እግዚእ። ፫ተ ጊዜያተ በል።

<u>ትዕዛዝ፡</u> በሥርዓት ዘደብር ዓባይ ወበከመ ተሠር
በወንበር ወእምድኅረዝ እቅድም ስብሐት ለከመ።

## <u>ስብሐተ አብ ዘሌሊት</u>

ዘበሰማያት **አቡነ** ወዘበምድር ዓዲ ግብተ
እንበለ ታኅንዲ ዘታብዕል ወዘታነዲ ስብ.ለከ።

**ይትቀደስ** ስምከ እግዚእ ዘኢትመወት ሕያው
በአፈ ኵሉ ፍጥረት በበመታልው በከላሕ
ወበንቃው ስብሐት ለከ።

**መንግሥትከ** ትምጻዕ እግዚእ ወሥምረትከ ሠ
ናይት ዕንተ ፈትውዋ በኵሉ ሰዓት ቀዳሚ
ማኅበረ ነቢያት ስብሐት ለከ።



ነቢያት ትንቢት እንደተናገሩ ኃጢአት ሳይኖርብህ ደዌያችንን የተቀበልክ መከራ ችንን የተሸከምክ አቤቱ ምስጋና ይገባሃል።

ኋላ በመንፈቅ ሌሊት ድንፋታ በሆነ ጊዜ ተሰብስበን በቤትህ እንኖር ዘንድ ተማጽነን በማለድንህ ጊዜ አቤቱ አቤቱ ክፈትልን።

3ት ጊዜ በል።

<u>መመሪያ፡</u>-በደብረ ዓባይ ሥርዓትና በወንበርም እንዳለው ተራ መጀመሪያ ስብሐት ለከመን ከዚያም ዘበሰማያት አቡነን በል። ነገር ግን ትደም ተከተሉ ከሌሎች የጸሎት ጊዜያት የተለየ እንዳይሆንና በሌሎችም አድባራት እንደሚባለው እንደሚ ከተለው ተቀምጧል።

## <u>በሌሊት የሚጸለይ የአብ ምስጋና</u>

በሰማይ የምትኖር ዳግመኛም በምድር ያለህ አባታችን ሆይ ሳትዘገይ ፈጥነህ የምታደኸይና የምታበለፅግ አቤቱ ምስጋና ይገባሃል።

አቤቱ የማትሞት ሕያው አምላክ ሆይ በፍጥረት ሁሉ እንደበት ባለማቋረጥ ስምህ ይቀደስ በጩኸትና በትጋት የምትመሰገን አቤቱ ምስጋና ይገባሃል።

ቀድሞ የነቢያት ማኅበር ሁልጊዜ ይመኙአት የነበረች የእማረች መውደድህና መንግሥትህ ትመጣልን ዘንድ አቤቱ ምስጋና ይገባሃል።

ፈቃድከ ይኩን እግዚእ ወሥምረትከ ውናይ
በምድር ወበሰማይ እግዚእ ወእዶናይ ስ.ለከ
ሲሳየነ ኩሎ ወዘሊብነ ይፈቱ እግዚእ ህበነ ጸ
በከንቱ ዘየእከል ለለዕለቱ ስብሐት ለከ።

አበሳነ ሥረይ እግዚእ ወዳኅፃቲነ እምሕ
ብዙኃ ምሕረት እምላክ ከመ ማየ ዐይግ የዋ
እንበለ ጹግ ስብሐት ለከ።

ከመ ንህነኒ ንኅድግ አበሳ ለዘቢጽነ አበ
ፍጥር ለነ እግዚእ ሕሊና ቅዱስ ወል
መስተፀግሠ ስብሐት ለከ።

ኢታብአነ እግዚእ ውስተ መንሱት ብዙ
ዘኢትመውት እምላክ ኖላዊ ትጉህ በሥር
ወበፍና ጉህ ስብሐት ለከ።

አድኅነነ ዘልፈ እግዚእ ለመልእከ ጽልመት
እምቀትሉ ወባልሐነ እምዕኩይ ኩሉ ለዓለ
እንተ ትሄሉ ስብሐት ለከ።



አቤቱ አሸናፊ እምላክ ሆይ የእግረች መውደድህና ፈቃድህ በሰማይና በምድር ትሆን ዘንድ ምስጋና ይገባሃል።

ልቦናችን የሚሻውን እንጀራችንን ሁሉ አቤቱ ለየዕለቱ የሚበቃንን ስጦታ ያለወጋ ትሰጠን ዘንድ ምስጋና ይገባሃል።

ያለቁጣ የዋህ የምትሆን ቸርነትህ እንደጉድጓድ ውሃ የበዛ እምላክ ሆይ ከሕግ ማዳጣችንን አይተህ አበሳችንን ታስተሰርይልን ዘንድ አቤቱ ምስጋና ይገባሃልቸ።

እኛም ወንድማችን የበደለንን በደል ይቅር እንል ዘንድ አቤቱ ታጋሽ ልብንና ለዩ ሃሳብን ትፈጥርልን ዘንድ እናመሰግንሃለን።

በጠዋትና በማታ መፈራረቅ የማታንቀላፋ ትጉህ ጠባቂ እምላክ ሆይ አቤቱ ወደፈተና እታግባን እያልን እናመሰግንሃለን።

ለዘለዓለሙ የምትኖር አቤቱ ከጭለማ ገዥ መጋደልና ከክፉ ነገር ሁሉ ዘወትር ታድነን ዘንድ ምስጋና ይገባሃል።

በኀዕለ ብዙኀ እድኀኖ ወዲበ ኵሉ ሰላም እስመ ዚአከ መንግሥት ኀይል ለዓለም ወለዓለም ሰ.ለከ ዘመሐረነ ወልድከ ጸሎተ ቅዱሳን እንግልጋ ሰበኒ ንጹሊ እንበለ ንትጋ እግዚእ ህበነ መንፈሰ ጸጋ ዘያሴኒ ኀዕለ ነፍስ ወሥጋ። ፫ተ ጊዜያተ።

## ስብሐተ ሥላሴ ዘሌሊት

ስብሐት ለከሙ ሥሉስ ቅዱስ እዕማደ ብሩኅ እሳት እስራኤልሃ እንበለ ዕቅፍት ዘመራሕ ከሙ ፍኖ ሌሊት ስብሐት ለከሙ።

እዕይንተ ሰብእ ሥላሴ ከመ ኢይድፍኖ ጽልመት እለ ታበርሁ በኵሉ ሰዓት ወርኃ ምስለ ከዋክብት ስብሐት ለከሙ።

ለምህሮ ትሥልስት ሥላሴ በሌሊተ ጥምቀት ሐዲስ ዘእስተርአይከሙ በዮርዳኖስ በእካል ዘይሜለስ ስብሐት ለከሙ።



ለዘለዓለሙ ኀይል መንግሥት የአንተ ነውና በብዙ ማዳንና በብዙ ይቅርታ ይቅር ትለን ዘንድ እናመሰግንሃለን።

ልጅህ ያስተማረንን የቅዱሳን ጸሎት ተሰብ ሰበን ያለ ማቋረጥ በምንጸልይበት ጊዜ እቤቱ ለነፍስና ለሥጋ የሚበጅ ሀብት ጸጋህን ስጠን።

፫ት ጊዜ በል።

## በሌሊት የሚጸለይ የሥላሴ

የብሩህ እሳት ምሰሶዎች ሥሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል እስራኤልን ያለእንቅፋት የሌሊት ጎዳናን የመራችሁ ምስጋና ይገባ ችኋል።

የሰውን ዓይን ጨለማ እንዳይሸፍነው ሌሊቱን ሁሉ ጨረቃን ከከዋክብት ጋራ የምታበሩ ስሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል።

ሦስትነትን ለማስተማር አዲስ በሚሆን በጥምቀት ሌሊት በሦስትነት እምሳል በዮርዳኖስ የተገለጻችሁ ስሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል።

በከመ ይትዔገስ እብ ሶበ ውሉዱ እበሱ
እምፍኖትከሙ ለዕለ ተግሕሡ ሥላሴ ዘትት
ዔገሱ ስብሐት ለከሙ።

እምጣነ ዕድሜየ ኃልቀ በእምሳለ ሕፃን
ጊጉይ እንዘ በጽቡር እትዋነይ ሥላሴ ዘምድር
ወዘሰማይ እንጽሑኒ በዘኢይደም ማይ።

፫ተ ጊዜያተ በል።

ስብሐት ለእግዚአብሔር ኪያነ ዘፈጠረ ከመ
ናምልኮ።

ስብሐት ለማርያም እመ እምላክ
እግዝእትነ ወመድኃኒትነ።

ስብሐት ለመስቀለ ክርስቶስ ዕፀ መድኃኒት
ኃይልነ ወጸወንነ።

ጸሎተ ሃይማኖት እስከ ሐመ ወሞተ በል።



አባት ልጆቹ በበደሉት ጊዜ እንደሚታገስ ከሕግ
ጎዳናችሁ የተለዩትን የምትታገሱ ስሉስ ቅዱስ
ሆይ ምስጋና ይገባችኋል።

እንደ በ ኛ ሕፃን በጭቃ ሥጋዬ ስጫወት
ዘመኔ አልቆአልና የሰማይና የምድር ገዢዎች
ስሉስ ቅዱስ ሆይ በኢድን ገንት ውሃ እንጹኝ።
3ት ጊዜ በል።

እናመልከው ዘንድ ለፈጠረን ለእግዚአብሔር
ክብር ምስጋና ይገባል።

እናታችንና መዳኛችን ለምትሆን አምላክን
ለወለደች ለማርያምም ክብር ምስጋና
ይገባታል።

አምባ መጠጊያችን ኃይላችንና የመዳን
እንጨት ለሚሆን ለክርስቶስ መስቀል ክብር
ምስጋና ይገባል። የሃይማኖት ጸሎት በል።

## ጸሎተ አባ ጊዮርጊስ ዘሰብዑቱ ጊዜያት

## ሰላመ ማርያም ዘነግህ

ሰላም ለኪ ማርያም ድንግል ዘመዐዛ አፉኪ ኮል እንተ ትጼንዊ በገዳም ወሐቅል ወልታ ረዲኤትየ በውስተ ቀትል ሰላም ለኪ።

ተሰፍዎ ባዕድ እልብየ ዘእንበሌኪ ምክሕየ በኢመንና በልኔ ጉብርየ ጉብርየ ዘተማየጥኩከ በንዋይየ ሰላም ለኪ።

እትሮንስ ሰሎሞን እንቲ ሊሖና ባሕርያ ንግሥታት ስሳ ወዕቁባት ሰማንያ ወደሳኪ እንዘ ይገንያ ሰላም ለኪ።

## የሰባቱ ጊዜያት የአባ ጊዮርጊስ ጸሎት

## በጠዋት የሚጸለይ የእመቤታችን ሰላምታ

የአፍሽ መዐዛ እንኮይ የሆነ በበረሃና በዱር የምትሸቺ ድንግል ማርያም ሆይ ሰላምታ ይገባሻል፤ በመከራዬ ጊዜ ረዳቴና ጋሻዬ ነሽና ሰላም እልሻለሁ።

መመኪያዬ እመቤቴ ሆይ ያለአንቺ ሌላ ተስፋ የማደርገው ዘመድ የለኝምና ባለመናቅ በገንዘቤ የገዛሁህ አገልጋዬ ወዳጄ ትይኝ ዘንድ ሰላም እልሻለሁ።

ሌሐና ዕንቋ የምትሆኚ የሰሎሞን ዙፋን እመቤቴ ሆይ ሰማንያ ዕቁባትና ስልሳ ንግሥታት እያገለገሉ እመሰግንውሻልና ሰላምታ ይገባሻል።

እመ ይከውን ድኅረ ዕለተ በቀል ወፍዳ
ወእመ ኢታድኅኒ እም ዘወለደት ወልዳ
ባልሕኒ እሞተ ዕዳ ሰላም ለኪ።
በከመ ልማድኪ በሊ ኀበ ወልድኪ ከሃሊ እ
ርኅሩኅ ኢተበቃሊ ያጠፍእኑ ለሥዕሉ
ሰዓሊ ኪነተከ ዘትካት ሐሊ። ፫ተ ጊዜያተ በል።

<u>ስብሐተ ኢየሱስ ዘነግህ</u>

ስብሐት ለከ ከመ ንንግር ኵሎ ስብሐቲከ
በእናቅጺሃ ለጽዮን ማኅደረ በዙኅ ሰላም
ዘእንቃሕከነ እምነ ንዋም ኢየሱስ ወልደ
ማርያም ስብሐት ለከ።



በኋላ ዘመን እናት የወለደቻትን ልጅ
በማታድንበት የፍዳና የበቀል ዕለት
በሚሆንበት ጊዜ ከሞት ዕዳ ታድኚኝ ዘንድ
ሰላም እልሻለሁ።
እንደልማድሽ ሁሉን ወደሚችለው ልጅሽ
እንዲህ በይ የማትበቀል ርኅሩኅ ሆይ ማይ
የሳለውን ሥዕል በከንቱ ያጠፋዋልን?
የቀድሞ ሥራህ አዳምን አስብ ብለሽ
አማልጂኝ። 3ት ጊዜ በል።

<u>በጠዋት የሚጸለይ የጌታችን ምስጋና</u>

የብዙ ፍቅር አንድነት ማደሪያ በምትሆን
በጽዮን በሮች ምስጋናህን ሁሉ እንናገር
ዘንድ ከእንቅልፍ ያነቃህን የማርያም ልጅ
ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ምስጋና ይገባሃል።

ላዕለ ጻድቃን ወኃጥአን ብርሃን ጸጋ ምዉቅ ዘታሠርቅ ለነ እምነ ምሥራቅ ኢየሱስ ፀሐየ ጽድቅ ስብሐት ለከ።

ለዘመጠነዝ ገብርከ ላዕሌሆሙ ፍድፍድና ጸጋ ወሀብት ፈደዩከ እኩየ እኪተ ሀየንተ ሠናይት ኢየሱስ ንጉሠ ስብሐት ስብሐት ለከ።

ኢየሱስ ሕሙይ በእንቲአነ ኢየሱስ ሙቁሕ እንተ ዐቀሙከ ውስተ አውደ ፍትሕ ጊዜ ኮነ ኅሐ ጽባሕ ስብሐት ለከ።

ከመ በግዕ የዋህ ወከመ ላሕም መግዝዕ መሥዋዕተ መድኃኒት ትኩን ለቤዝዎ ሰብእ ዘኃለፍከ ዐፀደ ግፍዕ ስብሐት ለከ።



በጻድቃንና በኃጥአን ላይ የሚሞቅ ብርሃንን ከወደ ምሥራቅ የምታወጣልን የእውነት ፀሐይ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ምስጋና ይገባሃል።

ይህንን ያህል የሀብት ብዛት በላያቸው ስለ አደረግህላቸው ስለ በጎ ፈንታ ክፉ ነገርን የከፈሉህ የምስጋና ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ምስጋና ይገባሃል።

የጎህ ንጋት በሆነ ጊዜ በፍርድ አደባባይ የአቆሙህ ስለእኛ የታሰርከ እስረኛ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ምስጋና ይገባሃል።

እንደ የዋህ በግና እንደ ተገዛ ላም ሰውን ሁሉ ለማዳን መሥዋዕት ትሆን ዘንድ በግፍ ቦታ ያለፍከ ጌታ ሆይ ምስጋና ይገባሃል።

እምልብነ እግኅሥ እግዚእ ነገረ ጸላኢ መሥሕት ዘአግሐሥከ ለነ ጽልመተ ሌሊት ኢየሱስ ብርሃነ ሕይወት ስብሐት ለከ።

፫ተ ጊዜያተ በል። በደብረ ዓባይ ብቻ።

አኰቴተ ስብሐት ወትረ ለመንግሥትከ ስቡሕ ጊዜ እምንቀምን ንነቅሕ ዘናቄርብ ለከ በቃለ ክሣሕ ወንፈሉ ስብሐተ ዘነግህ።

፫ተ ጊዜያተ። በደብረ ዓባይ ግን አንድ ጊዜ ብቻ ይባላል።

## ስብሐተ ሥላሴ ዘነግህ

ስብሐት ለከሙ ሥሉስ ቅዱስ መዋዕያነ ከልኤ እዕምሮ ለብርሃን በነግህ ዘፈጠሮ ቃልከሙ በተናግሮ ስብሐት ለከሙ።



የሌሊቱን ጭለማ ያስወገድክልን የሕይወት ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ አቤቱ የሚያስት የጠላት ነገርን ከልቦናችን ታርቅ ዘንድ እናመሰግንሃለን። 3ት ጊዜ በል።

ከእንቅልፋችን በነቃን ጊዜ ለተመሰገነው ጌትነትህ ዘወትር በጩኸት ቃል የምናቀርብልህ ፍጹም ምስጋና ነው። ዳግመኛም የጠዋት ምስጋናን እናቀርብልሃለን።

3ት ጊዜ በል።

## በጠዋት የሚጸለይ የሥላሴ ምስጋና

ቃላችሁ በመናገር ብርሃንን በነግህ የፈጠረው ሁለቱን እዕምሮ እምነትንና ክህደትን ድል የምትነሱ ስሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል።

እምነ ብርሃን ብርሃን መጠነ እሉቱ ስርናይ እለ እልበስክሙ ንገሥተ ሰማይ ለወርኅ ወለፀሐይ ስብሐት ለክሙ።

ሰዓተ ሌሊት ሥላሴ ዘወሰንክሙ በኃሕ ወዘአክበርክሙ በፀዳል ብሩህ ፀሐየ እምነ ወርኅ ስብሐት ለክሙ።

ኅበ ርኅራኄክሙ በዝኃ ወኅበ እልቡቱ መስፈርት እለ ተሰመዩ በስመ ብእሲት ሥላሴ ዕደወ ምሕረት ስብሐት ለክሙ።

ክመ ኀብረ ለይ ሥጋየ እመ በኃጢአት ቄሐ ሐዘን ብየ እምጣነ በዝኃ ሥላሴ ዘዮም ወዘእሜሃ በጽባሕ ሀቡኒ ፍሥሐሁ ጊዜያት በል።



ከብርሃን የሰንዴ ቅንጣት ታህል ብርሃንን ለጨረቃና ለፀሐይ ያለበሳችሁ የሰማይ ቱቶች ስሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል።

የሌሊቱን ሰዓት በጠዋት የወሰናችሁ ከጨረቃም ይልቅ ፀሐይን ብሩህ በሆነ ብርሃን ያከበራችሁ ስሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል።

ቸርነታችሁ ከበዛ ዘንድ ልክም የሌለው ከመሆኑ የተነሳ ቅድስት ተብላችሁ በሴት እንቀጽ የምትጠሩ የይቅርታ ጌቶች ስሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል።

ሥጋዬ በኃጢአት እንደ ቀይ ግምጃ በቀላ ጊዜ ሀዘንም በበዛብኝ ጊዜ የዛሬና የቀድሞ ጌቶች ስሉስ ቅዱስ ሆይ በጠዋቱ ደስታን ስጡኝ። 3 ጊዜ በል።

ጊዜ ጸልዮትኪ በጽሑ ሐመ ኢይሙት ገብርኪ ትድግሚዮ ሰግዱ ወአስተብርኪ እንዘ ታዜክርዮ እም ምግ ንግደትኪ ርግብየ የዋሂት ለየዋህ ወልድኪ። ፫ተ ጊዜያተ በል።

## ስብሐተ ኢየሱስ ዘሠለስቱ ሰዓት

ስብሐት ለከ እኤምኆ እዕጋሪከ በጊዜ ሠለስቱ ሰዓት ቅድመ ጲላጦስ ዘቆምከ ኢየሱስ ጻድቅ ወንጉሥ ፊማ ዘአድከምከ ኃይለ መስቴማ ስብሐት ለከ።

እንዘ ይሰልቡ ልብሰከ ወከዳንከ ጸዐዳ እንተ እልበስከ ከለሜዳ ኢየሱስ ንጉሠ ይሁዳ ስ.ለከ ተፈጸመ ብከ እግዚእ ቃለ ዳዊት ንጉሥ ሰበ ተካፈሉ በዕፃ ወፉስ ልብሰከ ልብሰ ምገስ ስ.ለ።



የዋሂት ርግብ እመቤቴ ሆይ እኔ አገይጋይሽ እንዳልሞት የምትጸልዩበት ሰዓት በደረሰ ጊዜ የስደትሽን ድካም ለደጉ ልጅሽ እያሳሰብሽው በፊቱ ፊዐመሽ ሰገጂ። ፫ት ጊዜ በል።

## የሦስት ሰዓት የጌታችን ምስጋና

የሰይጣንን ኃይል የአደከምከ እውነተኛ ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በሦስት ሰዓት በጲላጦስ ፊት የቆሙ እግሮችህን እጅ እየነሳሁ ምስጋናን አቀርብልሃለሁ።

ነጭ የሚሆን መጎናጸፊያህንና ቀሚስህን ገፈው ቀይ ግምጃ ያለበሱህ የይሁዳ ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ምስጋና ይገባሃል።

የክብር ልብስ በሚሆን ልብስህ ላይ ዕጣ ተጣጥለው በተካፈሉ ጊዜ አቤቱ የንጉሥ ዳዊት ቃል በአንተ ተፈጽሞአልና ምስጋና ይገባሃል።

ማኅበራነ አይሁድ አሜሃ አዕፅምቲከ ኆለቁ ወዲበ ገጽከ ምራቀ ወረቁ ላዕሌከ እንዘ ይሣለቁ ስብሐት ለከ።

እፎ መጠከ ዘባነከ ለጥብጣቤ መቅሰፍት በጸሀቅ ገጽከኒ ተወከፈ ሐፍረተ ምራቅ ዘአዕሩግ ወዘደቂቅ ስብሐት ለከ።

አዕርግ ለነ እግዚኦ በጊዜ ሠለስቱ ሰዓት ዘአቅረብነ ለከ መሥዋዕተ ስብሐት ሕገ ሠርዐ ሐዋርያት ስብሐት ለከ።፫ተ ጊዜያተ (በደብረ ዓባይ ብቻ)

ጎበ ሐዋርያት ኀብሩ በጽርሐ ጽዮን እንግልጋ ዘፈኖከ ሎሙ መንፈሰ ጸጋ ፈኑ ለነ እንበለ ንትጋ ያኀድገነ ምግባረ ዘሥጋ። ፫ተ ጊዜያተ በል።



ያንጊዜ የአይሁድ ማኅበር በአንተ ላይ እየተዘ ባበቱ አጥንቶችህን የቆጠሩ በፊትህም ላይ ምራቃቸውን የተፉብህ አቤቱ ምስጋና ይገባሃል።

ጀርባህን በሚያስጨንቅ የጅራፍ ግርፋት እንደ ምን ሰጠህ? ፊትህን የልጆችንና የሽማግሌዎችን የሐፍረት ምራቅ እንደምን ተቀበለ? አቤቱ ምስጋና ይገባሃል።

ሐዋርያት በሰሩት ሕግ በሦስት ሰዓት ያቀረብንልህን የምስጋና መሥዋዕት ታሳርግልን ዘንድ ምስጋና ይገባል። 3ት ጊዜ በል።

በጽዮን አዳራሽ ሐዋርያት በተሰበሰቡ ጊዜ የስጦታ መንፈስ ቅዱስን እንደላክላቸው ሥጋዊ ሥራን ያስተወን ዘንድ ያለማጉደል ላክልን።

3ት ጊዜ በል።

## ስብሐተ ሥላሴ ዘሠለስቱ ሰዓት

ስብሐት ለከ ሥሉስ ቅዱስ ጠበብተ ሰብዐቱ ዕለት አዳምሃ በሣልስት ሰዓት ዘፈጠርከ እንበለ ሞት ስብሐት ለከ።

ድኅረ ተፈጥሮቱ ለሰብእ በኁልቈ ዕለታት አርብዓ አለ ታንድዩ ወታብዕሉ ሰብአ መጽሐፍ ከመ እይድዓ ስብሐት ለከ።

ሐዋርያት ጽርሐ ሥላሴ በጊዜ ሰዓት ሠለስቱ በጬ ልሳን ወጀቱ ሥላሴከ ዘትከሥቱ ስብሐት ለከ።

ለጸላኤ ብርሃን ሰብእ ከመ ዘእኩይ ምግባሩ አለ ትሬእዩ ወትእምሩ ሥላሴ ዘትሚሕሩ ስብሐት ለከ።



## የሦስት ሰዓት የሥላሴ ምስጋና

አዳምን በሦስት ሰዓት ያለሞት የጠፈራችሁ የሰባቱ ዕለታት ጥበበኞች ሥሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል።

መጽሐፍ እንደተናገረው ሰው በተፈጠረ በአርባኛው ቀን በእናቱ ማኅፀን የምታስቀሩና የምታለመልሙ ሥሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል።

የቀን ብርሃን በርትቶ ሦስት ሰዓት በሆን ጊዜ በሰባ ሁለት ቋንቋ ሦስትነታችሁን የምትገልጹ የአብርሃም ቤት እንግዶች ሥሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል።

ብርሃንን የሚጠላ ሰውን ሥራው ክፉ እንደሆነ ፈጽማችሁ ስታውቁ ይቅር የምትሉ ሥሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል።

ድኅረ ስብከ ላሕም እቀመ በደብረ ኮሬብ መካነ ካህን አሮን ወምስመን ዘመሐርከምዎ ለአሮን ካህን መሐሩኒ ሥላሴ ኄራን።

፫ተ ጊዜያተ በል።

ይ.ሕ ስብሐት ለእግዚአብሔር በል። ጸሎተ ሃይማኖት።

## ሰላመ ማርያም ዘስድስቱ ሰዓት

ሰላም ለኪ ማርያም ውድስት በልሣነ ኩሉ ፍጥረት ታቦት እንቲ ዘሙሴ ጽላት ዘሕግ ወዘሥርዓት ሰላም ለኪ።

ገደብ ቡሩር ጽሩይ ወምቅድሐ ንጹሕ ሐሊብ ማርያም መሶብ ዘመና ልሁብ አንተ ፆርኪ ሲሳየ ሕዝብ ሰላም ለኪ።



ታማኝ የነበረ ካህኑ አሮን በኮሬብ ተራራ በላም አምሳል ጣኦት በአቆመ ጊዜ ካህን አሮንን ይቅር ያላችሁት ይቅር ባይ ስሉስ ቅዱስ ሆይ እኔንም ይቅር በሉኝ። ፫ት ጊዜ በል።

ለእግዚአብሔር ክብርምስጋና በል። የሃይማኖት ጸሎት።

## የስድስት ሰዓት የማርያም ሰላምታ

በሕግና በሥርዓት ያለች የሙሴ ጽላት ማደሪያ የምትሆኚ በፍጥረት ሁሉ አንደበት የምትመሰገኚ እመቤታችን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል።

የጠራ የብር ጽዋና የንፁሕ ወተት መቅጃ የሕዝብንም ምግብ የተሸከምሽ የትኩስ መና መሶብ እመቤታችን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል።

ትርሚተ ቤቱ ሠናይ ለነቢይ ሐጌ ወወለት እንቲ ዘሰሎሞን ሐርጌ ማርያም ዘመነ ጽጌ ሰላም ለኪ።

እመ ትድው በግዕ ዘሰቀልዎ በግፍዕ ወደብተራ ስምዕ ዘጳውሎስ ረድዕ ማርያም ዘመነ ፍግዕ ሰላም ለኪ።

እርያሬስ ሰማይ ልብስኪ ወአሳዕንኪ ዕብላ ጽጌ ደንጎላ ቀይሀ ዘምድረ ቆላ ማርያም ዘመነ ተድላ ሰላም ለኪ።

በመድበለ ማኅበር ጽፉቅ እዌድሰኪ በጻሕት ከመ ትምዕድኒ ነገራተ ጽድቅ ማርያም ዘመነ ዕርቅ ሰላም ለኪ።



የነቢዩ ሐጌ የእማረ የቤቱ ሽልማት የንጉሥ ሰሎሞን ውብ ልጅ እንቺ ነሽና የአበባ ዘመን እመቤታችን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል።

በግፍ የሰቀሉት ያማረ በግ እናቱ የሐዋርያው ጳውሎስም የምስክርነቱ ድንኳን የምትሆኚ የተድላና የደስታ ዘመን እመቤታችን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል።

ልብስሽ የሰማይ ፀሐይ ጫማሽም ጨረቃ የቆላ ምድር ቀይ የሱፍ አበባ ነሽና የደስታ ዘመን እመቤታችን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል።

የእውነት ምክሮችን ትመክሪኝ ዘንድ ብዙ በሆነ ማኅበር መካከል በትጋት እመሰግንሻለሁና የዕርቅ ዘመን እመቤቴ ሆይ ሰላም እልሻለሁ።

ተደንገፀ ሥጋ ወነፍስ ለባሕቲትኪ ኮነ እሙኒ በሥጋ ወለድኪ ሕጻነ ኢረሰሐ ወኢማሰነ ሰ.ኪ እሙ በሊዮ በእንቲአየ ለፍሬ ከርሥኪ እብኖዲ ላዕሌሁ ምሕረተ ኢታኅንዲ እመ አኀዘንከ ብእሲ አባዲ ቤዛ ነፍሱ ነፍስየ እፈዲ። ፫ተ ጊዜያተ

## ስብሐተ ኢየሱስ ዘስድስቱ ሰዓት

ስብሐት ለከ እ ዘተቀኖከ ኢየሱስ ጻድቅ ማዕከለ ክልኤ ፈያት እንዘ ኢትከውን እንተ ገባሬ እኪት ከመ ትሰዓር ቀኖተ ሞት ስ.ለከ። እድ ሰፋሕከ አዕጻወከ ወተቀኖከ በዕፅ ዕፀወተ ቀላያት ታርጉ እምሳለ እንቀጽ ዘሰፋሕከ በብሔረ ግብጽ ስብሐት ለከ።



ልጅን በሥጋ በወለድሽ ጊዜ ማኅተመ ድንግልናሽ ስለአላደፈና ስለአልተለወጠ የነፍስና የሥጋ መጠበት ለአንቺ ብቻ ሆኗልና እመቤታችን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል።

ለማህፀንሽ ፍሬ ለጌታ እናቱ ሆይ ሰነፍ ሰው በአሳዘነህ ጊዜ ስለሰውነቱ ድንት ሰውነቴን እከፍላለሁና ይቅርታህን እታዘግይበት በይው።

3ት ጊዜ በል።

## የስድስት ሰዓት የጌታችን ምስጋና

የሞትን ችንካር ትሽር ዘንድ አንተ ክፉ አድራጊ ሳትሆን በሁለት ወንበዴዎች መካከል የተቸነከርክ የእውነት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ምስጋና ይገባሃል።

በበር አምሳል የተዘጉ ወንዞችን ትከፍት ዘንድ በግብጽ ሀገር እጆችህን የዘረጋህ እጆችህን ዘርግተህ በእንጨት ላይ እንደምን ተሰቀልክ? አቤቱ ምስጋና ይገባሃል።

ፀሐይ ብሩህ እሜሃ ጊዜ ቀትር ጸልመ ወወርኀኒ
ንጹሕ ተመሰለደመ ትንቢት ከመ ቀደመ ሰ.ሰ
ከዚህ በታች ቀጥሎ የተጻፉት ቁጥሮች የደብረ ዓባይን
የአባባል ቅደም ተከተል ብቻ የሚያሳዩ ናቸው።

፩. ለአብርሃም አብ ቀዳሚ ዘአስተርአይከ
ክርስቶስ ቀትር ታሕተ ዕፀ ድርስ ተሰቀልከ
ከመ ዕቡስ ስብሐት ለከ።

፪. ኃዘን ማርያም እምከ ነጺረከ ለዘታፈቅር
ሐዋርያ ትቤሎ እምከ ነያ ትናዝዝ ብዝኃ ብካያ
ስብሐት ለከ።

፫. ዘሰአልከ ማየ እግዚእ እምነ ሳምራዊት
ብእሲት ከመ ትፈፅም ኲሎ ነገረ ትስብዕት
እንዘ አንተ ማየ ሕይወት ስብሐት ለከ።



አስቀድሞ ትንቢት እንደተነገረ ያንጊዜ ብሩህ
ፀሐይ በቀትር ሰዓት ጨለመ ንፁህ ጨረቃም
ደም መሰለ አቤቱ ምስጋና ይገባሃል።

1. አስቀድሞ ለአባት አብርሃም በቀትር ሰዓት
በወይራ እንጨት ስር የታየኸው ክርስቶስ
ሆይ እንደክፉ አድራጊ ተሰቅለሃልና
ምስጋና ይገባሃል።

3. የእናትህን ሀዘን አይተህ የልቅሶዋን ብዛት
ታረጋጋ ዘንድ ለምትወደው ደቀ መዝሙርህ
እነኋት እናትህ ያልከው አቤቱ ምስጋና
ይገባሃል።

2. አንተ የሕይወት መጠጥ ስትሆን ምስጢረ
ሥጋዊን ትፈጽም ዘንድ ከሳምራዊት ሴት
ውሃን የለመንከ አቤቱ ምስጋና ይገባሃል።

፪ ሕፅረነ ወትረ እግዚእ ለደቂቃ ዛቲ ማኅበር በመስቀልከ መግረሬ ፀር እምድድቅ ወእምጋኔነ ቀትር ወእምኵሉ ዘይመጽእ ግብር። ፫ተ ጊዜ።

ስብሐተ ሥላሴ ዘስድስቱ ሰዓት

ስብሐት ለከሙ ሥሉስ ቅዱስ ዕሩያን አካል ወገጽ ዘአስተርአይከሙ እንበለ ሕፀፅ ጊዜ ቀትር በታሕተ ዕፅ ስብሐት ለከሙ።

ለንግሥክሙ ሰገደ አብርሃም በርዕሱ ቤተ ገብርከሙ እንዘ ይብል ገሐሡ /እንዘ ትገይሡ/ እጋዕዝትየ ዘትኄልሱ ስብሐት ለከሙ።

በላዕለ ማርያም ድንግል ሥላሴክሙ ተረክበ ዮርዳኖስ ቅድመ ወበታቦር ካዕበ ወንጌል ከመ ነበበ ስብሐት ለከሙ።



4. አቤቱ ከሚጣላ ከቀትር ጋኔንና ከሚመጣ ሥራ ሁሉ የጠላት ማሸነፊያ በሚሆን በመስቀልህ የዚህችን ማህበር ልጆች ዘወትር አጠረን። 3ት ጊዜ በል።

በስድስት ሰዓት የሥላሴ ምስጋና

በቀትር ጊዜ በዛፍ ሥር ያለ ጉድለት የተገለጻችሁ በአካልና በገጽ የምትተካከሉ ስሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል.።

አብርሃም ከባሪያቸችሁ ቤት ግቡልኝ እያለ በራሱ ለንግሣችሁ የሰገደ ሦስትነት ያላችሁ ጌቶቼ ስሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል።

ወንጌል እንደተናገረ አስቀድሞ በዮርዳኖስ ዳግመኛም በደብረ ታቦር በድንግል ማርያም ላይ ሦስትነታችሁ የተገለፀ ስሉስ ቅዱስ ምስጋና ይገባችኋል።

ለቤተ ክርስቲያን ሥላሴ እናቅጺሃ እንትሙ ሱራፌልኒ በቅዳሴሆሙ ያዔምሩ ግጻዌክሙ ስ.ለ

ፈጣሪያነ ፀሐይ ወወርኅ አጋዕዝትየ ሥላሴ ዘነጸሩክሙ ኤልያስ ወሙሴ በስብሐት ወበ ውዳሴ ስብሐት ለክሙ።

ጠፈረ ቤትክሙ ማይ ዘኅብሩ በረድ እንተ ነጸርዎ ኅሩያን እዓጋድ በሲኢል ወበስጊድ ስብሐት ለክሙ።

እብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ለዝክርክሙ ሕይወት ሶበ ከናፍርየ እከሥት ስመ ዚእክሙ በኵሉ ሰዓት ይስማዕ እምእፉየ ወይደንግጽ ሞት
፫ተ ጊዜያተ በል። ስብሐት ለእግዚአብሔር በል።



ሱራፌል በምስጋናቸው ሦስትነታችሁን የሚያሳውቁ ለቤተ ክርስቲያን በሮቿ የምትሆኑ ሰሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል።

ኤልያስና ሙሴ በፍጹም ምስጋናቸው ያዩአችሁ ፀሐይና ጨረቃን የፈጠራችሁ ጌቶቼ ሰሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል።

የተመረጡ ወገኖች በጸሎትና በስግደት ያዩት ኅብሩ ነጭ የሚሆን የቤታችሁ ጣሪያ ውሃ ነውና ሰሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል።

እብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሆይ ሕይወት ለሚሆን ለስም እጠራራችሁ በየሰዓቱ ሁሉ ስማችሁን ለማመስገን እንደበቴን በከፈትኩ ጊዜ ሞት ከአፌ ሰምቶ ይደንግጥ።

3ት ጊዜ በል።
ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና በል።

## ሰላመ ማርያም ዘተሰዓቱ ሰዓት

ሰላም ለኪ ማርያም እከል ሰላም ለኪ መጽንዒተ ኃይል ሰላም ለኪ።

ቅብዐ ብርሃት ለገጽ ሰላም ለኪ ሰቴ ወይን ዘንፈርዓጽ ሰላም ለኪ።

ሠርጉ ክብር ዐራዝ ሰላም ለኪ ወመቅደስ ቤተ ትዕዛዝ ሰላም ለኪ።

ቁጥሮቹ የደብረ ዓባይን የአባባል ቅደም ተከተል የሚያሳዩ ናቸው።

፩. ለእማዕንኪ ወርኅ ሰላም ለኪ ወለእክሊልኪ ጎሐ ጽባሕ ሰላም ለኪ።

፪. ደመና ዝናም ንጽሕት ሰላም ለኪ ዘይከውን ለቅድሳት ሰላም ለኪ።

፫. ወለተ ኢያቄም ወሐና ሰላም ለኪ ሥርጉት በቅድስና ሰላም ለኪ።

## ቀን በዘጠኝ ሰዓት የእመቤታችን ሰላምታ

እሀል እመቤታችን ሆይ ኃይልን የምታጸኚ ሰላምታ ይገባሻል።

ለፊት ብርሃን ቅባት የደስታ መጠጥም የምትሆኚ ወይን እመቤታችን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል።

የክብር ሽልማት መጎናጸፊያ የትዕዛዝ ቤት መቅደስም እመቤታችን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል።

ከዚህ በታች ተጥሎ የተጻፉት ቁጥሮች የደብረ ዓባይን የአባባል ቅደም ተከተል ብቻ የሚያሳዩ ናቸው።

1. ጫማሽ ጨረቃ አክሊልሽም የጎሕ ንጋት እመቤታችን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል።

4. ለንጽህና የሚሆን የንጹሕ ደመና ዝናም እመቤታችን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል።

5. የሐናና የኢያቄም ልጅ በንፅህና የተዋብሽ እመቤታችን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል።

፪. ደብረ መድኃኒቱ ለኖኅ ሰላም ለኪ ዘኃባ ዕኪዮ እግዮ እድኅ ሰላም ለኪ።

፫. ሐይመተ አብርሃም አብ ሰላም ለኪ ዘኮንኪዮ ከመ ተድባብ ሰላም ለኪ።

፮. ቤዛዊተ ኵሉ ዓለም ሰላም ለኪ ሰብሐት በአርያም ሰላም ለኪ ።

፯. ያሰምዐኒ ቃለ ፍሥሐ ጊዜ በሐዘን እስቀቁ ማህልኪ ይምጻእ እምሥራቅ ለእሳተ ሐዘን እስከ ይቀርር ሞቁ ማርያም ለኃጥእ ጽድቁ።
፫ተ ጊዜያተ።

<u>ሰብሐተ ኢየሱስ ዘተሰቅለ ሰዓት</u>

ሰብሐት ለከ እምላኪየ እምላኪየ ነጽረኒ ወትሬ ወኢትገድፈኒ ዘለፈ እስመ እንተ ትቤ እንዘ ትከ ሥት አፈ ትፈጽም ሕገ ዘተጽሕፈ ሰብ.ለከ።



2. ከጥፋት ውሃ የሰወርሽው የኖኅ የድኅነት ተራራ እመቤታችን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል።

3. የአባት አብርሃም ድንኳን እንደ ድባብ የሆንሽው እመቤ ታችን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል

6. የዓለም ሁሉ · መድኃኒት በሰማይ የምትመሰገኚ እመቤታችን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል።

7: በሐዘን በማለቅስ ጊዜ የደስታን ቃል ያሰማኝ ዘንድ የኃጢአተኛ ጽድቁ እመቤ ታችን ሆይ የሀዘን እሳት ማቃጠሉ እስኪበርድ ድረስ ይቅርታሽ ከምሥራቁ ይምጣ። 3ት ጊዜ።

<u>የዘጠኝ ሰዓት የጌታችን ምስጋና</u>

የተጻፈውን ሕግ ትፈጽም ዘንድ አንተ አፍህን ገልጠህ እንደተናገርክ አምላኬ አምላኬ ዘወትር ተመልከተኝ ፈጽመህም አትተወኝ እያልኩ ምስጋናን አቀርብልሃለሁ።

፩. ጊዜ ትወጽእ ነፍስከ እስከ ይሰማዕ ኩሉሂ ዘትቤ ኤሎሄ ኤሎሄ ኢየሱስ አምላክ ርኅራኄ ስብሐት ለከ።

፪. ከመ ተሀበነ ለነ ደመ ገቦከ ነባቢ አንተ አስተዩከ ሓሞተ ወከርቤ ጸማዕከ ዘእመ ትቤ ስብሐት ለከ።

፫. ድኅረ ሰለጥከ መዊተ በመልዕልተ ቅዱስ ጸልቦ እጓዚ ላዕሌከ ኃጢአት አልቦ ኢየሱስ ርጉዘ ገቦ ስብሓት ላኪ።

፬. ስታየ ጽሙዓን ይኩን ወዘያረስዕ ትካዘ ማይ ምስለ ደም ውኅዘ ገቦከ ጊዜ ተረግዘ ስብ.ለኪ።

፭. ኖላዊነ ኄር ወዐቃቢነ ጽኑዕ አንተ ተሰቀልከ መልዕልተ ምሥዋዕ ኢየሱስ ቤዛ አባግዕ ስ.ለከ



ነፍስህ ከሥጋህ በምትለይበት ጊዜ በሁሉ እስኪሰማ ድረስ ኤሎሄ ኤሎሄ እያልክ የጸለይክ ደግ ቸር አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ምስጋና ይገባል።

3. ከላሽ የሚሆን የጎንህን ደም ትሰጠን ዘንድ ተጠማሁ በአልክ ጊዜ ሐሞትና ከርቤ ያጠጡህ አቤቱ ምስጋና ይገባሃል።

2. በላይህ ኃጢአት ሳይኖርብህ በክቡር መስቀል ላይ ሞትን ከፈጸምክ በኋላ ጎንህን የተወጋህ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ምስጋና ይገባሃል።

4. ለተጠሙት መጠጥ ሀዘንንም የሚያስረሳ ይሆን ዘንድ ጎንህን በተወጋህ ጊዜ ውሃ ከደም ጋራ የፈሰሰህ አቤቱ ምስጋና ይገባሃል።

5. ቸር እረኛችን ጽኑ ጠባቂያችንም ስትሆን በመስቀል ላይ የተሰቀልክ የምዕመናን ቤዛ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ምስጋና ይገባሃል።

ተወከፍ ሊተ እግዚኦ ከመ ቊርባን ጥሉል በበሱባዔ እንዘ እከፍል ዘአቅረብኩ ለከ ጉልቄ ኢዮቤል ሰብሓታተ በዘእንበ እከል። ፫ተ ጊዜያተ።

## ስብሐተ ሥላሴ ዘተሰዓቱ ሰዓት

ስብሓት ለከሙ ሥሉስ ቅዱስ ንግሥተ ሰብዑቱ ዐብያት እለ በላዕክሙ ውሣጤ ሐይመት አሐደ ኀብሰተ ትሥልስት ስብሐት ለከሙ።

ድኀረ በላዕክሙ ሳሕም በእንተ ፍቅሩ ሰብእ ፍጹም ዘበኃይልክሙ ሐይወ ሳሕም ሥላሴ ክቡራን ስም ስብሐት ለከሙ።

ከመ ባሕር ስፉሕ ወከመ እሳት ድዱል እለ አርአይክሙ/እንዘ ብክሙ/ ትሥልስተ አካል ሥላሴ ንግሥተ ኃይል ስብሐት ለከሙ።



እኔ በምችለው መጠን በሰባቱ ጊዜያት እየከፈልኩ በኢዩቤልዩ አቆጣጠር ልክ ያቀረብኩልህን ምስጋና አቤቱ እንደለመለመ ቊርባን አድርገህ ተቀበለኝ። 3ት ጊዜ በል።

## የዘጠኝ ሰዓቱ የሥላሴ ምስጋና

የሰባቱ ሰማያት ጌቶች ሥሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል። ለአንድነታችሁ ምሳሌ የሚሆን ሦስትነታችሁ አንድ ኅብስት በድንኳን ውስጥ የተመገባችሁ ምስጋና ይገባችኋል።

ፍጹም ስለሚሆን ስለሰው ፍቅር የወይፈን ፍሪዳን ከተመገባችሁ በኋላ ወይፈኑ በኃይላችሁ ተነስቶአልና በስም አጠራራችሁ የከበራችሁ ሥሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል።

እንደ ባሕር የሰፋ እንደ እሳትም የበራ የአካል ሦስትነት ያሳችሁ የኃይል ንግሥታት ሥሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል።

ዘኢ ... ወኢትትመዐዑ ዘልፈ እን።
ሰብእ ይገብር ኃጣውእ እልፈ ሥላሴ ከመ
ተጽሕፈ ሰብሐት ለከሙ።

ሙላ/ ለቡርኩ ዴወወ በፍቅረ እሑቲ ብእሲት
ለዘወጽእ ረድዕ እምሃይማኖት ዘመሐርከምዎ በዕ
ስራ ዕለት መሐሩኒ ሥላሴ ንገሥት። ፫ተ ጊዜያተ።
ሰብሐት ለእግዚአብሔር በል። ጸሎተ ሃይማኖት በል።

## ሰላመ ማርያም ዘሠርክ

ሰላም ለኪ ምልዕተ ጸጋ ምልዕተ ክብር
ወብዕል እንበለ ንትጋ እምላከ ሰማያዊ
ዘወለድኪ በሥጋ።



ሃስትንታችሁ በመጽሐፍ እንደ ተጻፈ ሰው
ብዙ ኃጢአት ሲሰራ ዘወትር የማትቆጡና
የማትቀሰፉ ስሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና
ይገባችኋል።

ከሃይማኖት የወጣውን ደቀ መዝሙር በእንዲት
ሴት ፍቅር ልቦናውን ከማረከ በኋላ በሃያኛው
ቀን ይቅር ያላችሁት የይቅርታ ንጉሥታት
ስሉስ ቅዱስ ሆይ እኔንም ይቅር በሉኝ። ፫ትጊዜ።
ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና በል። የሃይማኖት ጸሎት በል።

## በማታ የሚጸለይ የእመቤታችን ምስጋና

ጸጋን የተመላሽ ብልጽግናንና ክብርን
ያለጉድለት ያገኘሽ መቤታችን ሆይ ሰማያዊ
ንጉሥን በሥጋ ወልደሻልና ሰላምታ
ይገባሻል።

ሰላም ለኪ ታቦተ ሕግ እንቀጸ ሥጋኪ ዘበ ድንግልና ንሡግ ሐሊበኪ ጠበወ እበ እዕሩግ ዘየዐውድዎ ዘወንጌል እፍላግ።

ሰላም ለኪ (እ) እግዝእትየ እሙ ለፀሐይ ጻግሚት ሰማይ መዝገበ ሥርናይ ወዘወይን ቀላይ ብኪ ወበወልድኪ ይብዕል ነዳይ።

ሰላም ለኪ ሐመረ ብዕል ሙዳየ ዕፍረት ቢረሌ ፅዱል ምዕራፈ ተድላኪ በብሔር ጥሉል መልክዐ ገጽኪ በአርያም ሥዑል።

ሰላም ለኪ እመ ብርሃን ዘወለድኪ ለነ ብሉየ እዝማን ለኪ ወለወልድኪ ይገኒ ልሣን።

ሰላም ለኪ ሰላማዊት ዘበድንግልና ኀትምት ወበቅድስና ሥርጉት ንህብ ዘእስኔት ወዘሲና ዕፀት።



የሥጋሽ በር በድንግልና ቁልፍ የተቆለፈ የሕግ ማደሪያ ሆይ የወንጌል ወንዞች የሚዞሩት የሽማግሌዎች እባት ጡትሽን ጠብቶእልና ሰላምታ ይገባሻል።

ለፀሐይ እናቱ ሁለተኛ ሰማይ እመቤቴ ሆይ ሰላምታ ይገባሻል። የወይን በር የስንዴ ሳጥን ነሽና፡በእንቺና በልጅሽ ድሀ ይበለፅጋል።

የጠራ ብርሌ የሽቶ ሙዳይ የምትሆኚ የብልፅግና መርከብ ሆይ ሰላምታ ይገባሻል። የተድላና የደስታ መኖሪያሽ በለመለመ ሃገር ነው የፊትሽም መልክ በሰማይ የተሳለ ነው።

ዘመናትን የሚያሳልፍ ጌታን የወለድሽልን የብርሃን እናቱ ሆይ ሰላምታ ይገባሻል። ለእንቺና ለልጅሽ እንደበት ይገዛል።

በንጽሕና የተሸለምሽ በድንግልናም የታተምሽ ሰላማዊት ሆይ ሰላምታ ይገባሻል። የንብ እመቤት የደብረ ሲናም ዕፅ ነሽ።

ሰላም ለኪ ታቦተ ሙሴ እምእመ ንእስኪ ዘኢተአምረ ብእሲ ወሐውልተ ስምዕ ዘነቢይ እሙሴ ለኪ ወለወልድኪ ይደሉ ውዳሴ።

## ስብሐተ ኢየሱስ ዘሠርክ

ስብሐት ለከ ሀበነ ሰላመከ መምሀረ ትሕትና ክርስቶስ ወልደ እምላክ ወሰብእ ጊዜ ፍና ሠርክ በዐውደ መብልዕ ዘረፈቀ ምስለ እርዳዕ ስብሐት ለከ።

ሥጋከ ቅዱስ ለወጢነ ሐዲስ ሥርዓት እንተ ወሀብኮሙ ለሐዋርያት ድኅረ በልዑ ፍሥሐ እሪት ስብሐት ለከ።

እምሥጢርከ ይንስኡ ኀበ ሐዋርያት ኃብሩ እንተ እዘዝኮሙ እምድኅረ ተደሩ ተዝካረከ ከመ ይግበሩ ስብሐት ለከ።



ከታናሽነትሽ ጀምሮ ወንድ የማታውቂ የሙሴ ጽላት ሆይ ሰላምታ ይገባሻል። እሙሴ የተባለ የነቢዩ የኢያሱ የምስክርነቱ ሐውልት ነሽና እመቤቴ ሆይ ለአንቺና ለልጅሽ ም. ይገ።

## በማታ የሚጸለይ የጌታችን ምስጋና

የሰውና የእምላክ ልጅ የትሕትና መምህር ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ሰላምህን ስጠን። በማታ ጊዜ ከደቀ መዛሙርትህ ጋራ በማዕድ የተቀመጥከ አቤቱ ምስጋና ይገባሃል።

የፋሲካን ቂጣ ከበሉ በኋላ አዲስ ሥርዓትን ለመጀመር ለደቀ መዛሙርትህ ቅዱስ ሥጋህን የሠጠሃቸው ምስጋና ይገባሃል።

ከምሥጢርህ ይቀበሉ ዘንድ ሐዋርያት በተሰበሰቡ. ጊዜ ሥጋህን ከተቀበሉ በኋላ መታሰቢያህን ያደርጉ ዘንድ ያዘዝካቸው አቤቱ ምስጋና ይገባሃል።

በእንተ ይሁዳ ዘትቤ ያገብእኒ እሐዱ ተሰዕሎተ ዝንቱ ነገር ለእለ ፈቀዱ ዘእርእ ይኩሙ ርደተ ዕዱ ስብሐት ለከ።

ለውእቱ አብድ እንተ እፍቀረ ዕበደ እምኀየሰ ሶበ ኢተወልደ እምያገብዕከ በዘ ፈቀደ ስብሐት ለከ።

በዛቲ ሰዓት በእዕዳዊ ክልኤ ጸድቃን እንተ ተገንዝከ/ገነዙከ/ በእምሳለ በድን ኢየሱስ መንሰዔ ሙታን ስብሐት ለከ።

ዘንተ ኵሉ በእንተ ፍቅረ ሰብእ ዘኮንከ ለሕማም ወሞት እስከ በጺሕከ ይእዜኒ ተወከፍ ነግሀ ወሠርክ ስብሐታተ ዘአቅረብነ ለከ። ፫ተ ጊዜ

### ስብሐተ ሥላሴ ዘሠርክ

ስብሐት ለከ ሥሉስ ቅዱስ መገብተ ሰማያት ዐበይት ዘትሁቡ ዐስበ በሠርክ ሰዓት ለቀደምት ወለደኀርት ስብሐት ለከ።



ስለ ይሁዳ ስትናገር ከእናንተ አንዱ ያስይዘኛል በአልክ ጊዜ ይህን ነገር ለመጠየቅ ለወደዱ የእጁን ወደ ወጪት ማውረድ ያሳየሃቸው ምስጋና ይገባሃል።

ስንፍናን ለወደደ ለዚህ ሰነፍ ሰው ሊያስይዝህ በወደደ ጊዜ ባይወለድ ይሻለው ነበርና ያልከው ምስጋና ይገባሃል።

በዚህች ሰዓት በሁለቱ ደጋግ ሰዎች እጅ በበድን አምሳል የተገነዝክ ሙታንን የምታነሳቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ምስጋና ይገባሃል።

ለሕማምና ለሞት እስከትደርስ ድረስ ስለሰው ፍቅር ይህን ሁሉ የሆንክ ሆይ አሁንም ጠዋትና ማታ ያቀረብንልህን ምስጋና ተቀበል። 3ት ጊዜ።

### በማታ የሚጸለይ የሥላሴዎች ምስጋና

ለኋለኞችና ለፊተኞች የዕለት የዕለት ምግብን የምትሰጡ የታላላቆቹ ዓለማት መጋቢዎች ስሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል።

ውስተ መዐርጋት ዐሠርቱ ዘአግባዕከሙ ፀሐየ ሶበ ኀቤከሙ ጊዜ ሠርክ ጸለየ ሕዝቅያስ እንተ ደወየ።

ጊዜ ጸልዮ ሥላሴ በአዕዛነ መንፈስ ዕፁብ እለ ትሰምዑ ለሆሳሰ ልብ ወትጸመሙ ብዝኃ ንባብ።

በይነ ሥጋዊ ሲሳዩ ወመንፈሳዊ ሲሳዩ ለዘርኀብ ሰብእ እምጌጋዩ ሥላሴ ዘትሔልዩ ሰ.ለከሙ።

ጊዜ ፍና ሠርክ ዳዊት ኣመ ውስተ ናሕስ ቆመ ሠለስተ ግብራተ ድኅረ ፈፀመ ዘመሐርከምዎ ለዳዊት ቅድመ መሐሩኒ ሥላሴ ዳግመ።

፫ተ ጊዜያተ። ስብሐት ለእግዚአብሔር በል።



የታመመው ሕዝቅያስ በሠርክ ሰዓት ወደ እናንተ በጸለየ ጊዜ ፀሐይን ወደ አሥረኛው ደረጃዎች የመለሳችሁ ስሉስ ቅዱስ ሆይ ም. ይገ።

በጸሎት ጊዜ ድንቅ በሚሆን በመንፈሳዊ ጆሮ ጸሎተ ሕሊናን የምትሰሙ የነገርን ብዛት ቸል የምትሉ ስሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል።

በሥጋዊና በመንፈሳዊ ምግብ በበደሉ ምክንያት ለተራበ ሰው የምታስቡ ስሉስ ቅዱስ ሆይ ም. ይገ።

ዳዊት በሠርክ ጊዜ በሰገነት ላይ ቆሞ ሦስት ሥራዎችን ከፈፀመ በኋላ ቀድሞ ዳዊትን የማራች ሁት ስሉስ ቅዱስ ሆይ ዳግመኛ እኔንም ማሩኝ።

3ት ጊዜ በል። ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና በል። የፃ. ጸሎት ።